# በብልፅግና ፓርቲ

# መተዳደሪያ ደንብ ላይ የተደረጉ ማሻሻያዎች

**(በማዕከላዊ ኮሚቴ ተቀባይነት ያገኘ)**

**ታህሳስ 2017 ዓ.ም**

**ብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት**

**አዲስ አበባ**

# በመተዳደሪያ ደንብ የተሻሻሉ ድንጋጌዎች

| ተ.ቁ | አንቀጽ | መሻሻል ያስፈለገበት ምክንያት | የተሻሻሉ ድንጋጌዎች |
|---|---|---|---|
| 1. | **አንቀጽ 2 ትርጓሜ - አዲስ** | መተዳደሪያ ደንብ ተከትለው እየወጡ ያሉት መመሪያዎች ለተለያዩ ቃላት የተለያዩ ትርጓሜ እየተሰጠ ስለሆነ ወጥ ትርጓሜ እንዲኖራቸው ለማድረግ፣ | አዲስ አንቀጽ - በመተዳደሪያ ደንቡ ለወጥነት የሚከተሉት ቃላቶች ትርጓሜ እንዲኖራቸው ተደርጓል፡-<br>• ፓርቲ፣ ጉባዔ፣ ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንቶች፣ የብልፅግና ምክር ቤት፣ ኮሚሽን፣ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፣ ዋና ጽ/ቤት፣ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች፣ አስተባባሪ ኮሚቴ፣ ኮንፈረንስ፣ ክልል፣ ዞን/ከተማ/ወረዳ፣ የብልፅግና ህብረት፣ የብልፅግና ቤተሰብ፣ አባል፣ እጩ አባል፣ አመራር፣ ክንፍ፣ ደጋፊ፣ የክብር አባል፣ ሥነ-ምግባር፣ የአባል ምልመላ፣ የአባል ግንባታ፣ ምዘና፣ ስንብት፣ ቅሬታ፣ አቤቱታ፣ |
| 2. | **በሰነዱ ውስጥ** | • የማዕከላዊ ኮሚቴ፣<br>• የኢንስፔክሽንና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን<br>• መሰረታዊ ድርጅት፣<br>• ህዋስ<br>• የኮሚሽን “ሰብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢ” እና<br>• ሊጎች የሚለው | • የብልጽግና ምክር ቤት፣<br>• የማዕከላዊ የኢንስፔክሽንና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን<br>• የብልፅግና ህብረት፣<br>• የብልፅግና ቤተሰብ፣<br>• የኮሚሽን “ዋና ኮሚሽነር እና ምክትል ዋና ኮሚሽነር” እና<br>• ክንፍ በሚል ተተክቷል፣ |
| 3. | **አንቀጽ 7 የፓርቲው ዓላማዎች፣ መርሆዎችና እሴቶች የአሰራር ሥርዓቶች** | አንቀጽ 7(3) (ሰ) የፓርቲው እሴቶች ላይ | • “አካታችነት” የሚል ቃል ተጨምሯል፡፡ |
| 4. | “ | • በንኡስ አንቀጽ 4(ቀ) አባላት በስብሰባዎች የመገኘት ግዴታ አለባቸው ከሚል በስተቀር፣ ማንኛውም የፓርቲ ሙሉ እና እጩ አባላት በህዋስና መ/ድርጅት ተደራጅተው መንቀሳቀስ እንደሚገባ አለመቀመጡ፣ | • የንዑስ አንቀጽ (ቀ) ማስተካከያ - ሁሉም የፓርቲ ሙሉ እና እጩ አባላትና አመራር በብልፅግና ቤተሰብ እና ብልፅግና ህብረት አደረጃጀቶች ተደራጅተው የመንቀሳቀስ እና በየደረጃው በሚካሄዱ ኮንፈረንሶችና ስብሰባዎች የመገኘት ግዴታ አለባቸው፣ በሚል ተስተካክሏል፡፡ |

| ተ.ቁ | አንቀጽ | መሻሻል ያስፈለገበት ምክንያት | የተሻሻሉ ድንጋጌዎች |
| --- | --- | --- | --- |
| 5. | “ | ➢ በንኡስ አንቀጽ 4(ዠ) - የእውቅናና ሽልማት አሰራር ግልጽ አለመሆኑ፣ | ➢ የንዑስ አንቀጽ (ዠ) “ፓርቲው ለአባላቱ፣ አመራሩና መዋቅሩ ላሳዩት የላቀ አፈጻጸም የተሻለ አስተዋጽኦ ላበረከቱ፣ ለህዝብ የጎላ ፋይዳ ያላቸውን ተግባራት ላከናወኑ እና ረዘም ላለ ጊዜ በፓርቲ ውስጥ የላቀ ተግባር ለፈጸሙ አባላት እውቅናና ሽልማት ይሰጣል፡፡ ዝርዝር መመሪያው በብልፅግና ምክር ቤት ይወጣል” በሚል ተስተካክሏል፡፡ |
| 6. | **አንቀጽ 8 የፓርቲ የምርጫ መርህና የአሰራር ሥርዓት** | በጠቅላላ፣ የአከባቢ፣ የማሟያ እና የድጋሚ ምርጫዎች በየደረጃው የሚገኘው የፓርቲ አባላት፣ አመራርና መዋቅሮች ሚና አለመቀመጡ፣<br>የፓርቲ ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዳንቶች ምርጫ በግልጽ መደንገግ እንዳለበት በምርጫ ቦርድ አስተያየት በመስጠቱ፣<br>የምርጫ ሂደቶች ማለትም የእጩ ጥቆማ፣ በሚስጢር ድምጽ አሰጣጥ፣ ድምጽ ቆጠራ፣ ውጤት መደመርና ውጤት አገላለጽ በግልጽ እንዲቀመጥ በምርጫ ቦርድ አስተያየት በመስጠቱ፣ | 1. ንዑስ አንቀጽ (4) “በጠቅላላ፣ የአከባቢ፣ የማሟያ እና የድጋሚ ምርጫዎች በየደረጃው የሚገኘው የፓርቲ አባላት፣ አመራርና መዋቅሮች ሚና ብልፅግና ምክር ቤት በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይወሰናል” የሚል አዲስ ተጨምሯል፡፡<br>2. የፓርቲ ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዳንቶች ምርጫ ሂደት በአስመራጭ ኮሚቴ የሚከናወን መሆኑና የአስመራጭ ኮሚቴ አመሰራረት፣ ተግባርና ሃላፊነቱ እንዲገባ ተደርጓል፡፡<br>3. የምስጢር ድምጽ አሰጣጥ፣ ድምጽ ቆጠራ፣ ውጤት መደመር፣ ውጤት አገላለጽ ሂደቶች በቴክኖሎጂ በታገዘ የምስጢር ድምጽ አሰጣጥ ጥቅም ላይ እንደሚውልና ዕክል በሚያጋጥምበት ጊዜ በኮሮጆ የምስጢር ድምጽ አሰጣጥ ዘዴ ተግባራዊ እንደሚደረግ ተቀምጧል፡፡ |
| 7. | **አንቀጽ 10 ለአባልነት የሚቀርብ ጥያቄ** | 1. በንኡስ አንቀጽ (3) ስድስት ወር የሙከራ ጊዜ አጭር በመሆኑ የጥራት ችግር ማስከተሉ፣<br>2. አባል ሲሆን መሃላ የሚፈጽምበት ስርዓት አለመኖር፣ | 1. በንኡስ አንቀጽ (3) “በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት መስፈርቱን አሟልቶ የተመለመለ ግለሰብ ለስድስት ወራት በደጋፊ አባልነት እና ለስድስት ወር በዕጩ አባልነት መቆየት አለበት” በሚል ተሻሽሏል።<br>2. አዲስ ንዑስ አንቀጽ (6) “እጩ የሆነ አባል የፓርቲውን ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብና የፓርቲውን ዲስፕሊን አውቆ ከተቀበለ በኋላ በፓርቲ አባላት ኮንፈረንስ ፊት መሃላ ይፈጽማል” በሚል ተጨምሯል፣ |

| ተ.ቁ | አንቀጽ | መሻሻል ያስፈለገበት ምክንያት | የተሻሻሉ ድንጋጌዎች |
|---|---|---|---|
| 8. | **አንቀጽ 11(1) የአባል መብት** | 1. የአባልነት ማረጋገጫ መታወቂያ የማግኘት መብት አለመቀመጡ፣<br><br>2. የፓርቲ አባላት በክብር የሚሸኙበት አሰራር አለመኖር፣ | • አዲስ ንዑስ አንቀጽ (ሸ) - የአባልነት መታወቂያ የማግኘት መብት አለው'' የሚል ተጨምሯል፣<br>• አዲስ ንዑስ አንቀጽ (3) "የፓርቲ አባላት በክብር የሚሸኙበት፣ በክብር እና በፍቃደኝነት የተሰናበቱ አባላትን ፓርቲው ልምዳቸውን የሚጠቀምበት የአሰራር ስርዓት በብልፅግና ምክር ቤት በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፤ በሚል ተጨምሯል። |
| 9. | **አዲስ አንቀጽ -አባልነት ስለማቋረጥ** | ንኡስ አንቀጽ (1)(ሰ) አባል ከፓርቲው የሚለቅበት መንገድ በፈቃደኝነት ብቻ አድርጎ ያስቀመጠ በመሆኑ የተሟላ አለመሆኑ፣ | አዲስ አንቀጽ 13 - አባልነት ስለመቋረጥ:-<br>• በራስ ፍላጎት፣<br>• በክብር በመሰናበት፣<br>• በሞት፣<br>• የሌላ ፓርቲ አባል ሆኖ ስገኝ፣<br>• በህግ መብቱ ሲገድብ እና<br>• በዲሲፕሊን ቅጣት ከአባልነት ይሰናበታል፡ በሚል ተቀምጧል። |
| 10. | **አንቀጽ 13 በአባላት ላይ ስለምወሰዱ እርምጃዎች** | 1. በዲሲፕሊን ጉድለት የሚወሰድ እርምጃ እንጂ የፓርቲ ዲሲፕሊን ስለማክበር አለመቀመጡ፣ | 1. አዲስ ንዑስ አንቀጽ(1) – "ማንኛውም የፓርቲ አባል በሚመለከተው የፓርቲ አካል የወጣ የዲሲፕሊን መመሪያ/ዎችን የማክበር ግዴታ አለበት'' በሚል ተቀመጧል። |
| 11. | **አንቀጽ 16 የፓርቲ ጉባዔ** | የጉባዔ ለ6 ወራት ጊዜ ማረዘም የሚወስን አካል አለመቀመጡ እና ንዑስ አንቀጽ ሁለት የተለያዩ ሀሳቦች የያዘ በመሆኑ መለየት በማስፈለጉ፣ | ንዑስ አንቀጽ (1) – "የፓርቲው ጉባዔ በየሁለት ዓመት ተኩል አንድ ጊዜ ይካሄዳል''፣<br>ንዑስ አንቀጹ (3) "በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መደበኛ ጉባዔውን መጥራት የማይቻልበት አስገዳጅ ሁኔታ ሲያጋጥም የብልፅግና ምክር ቤቱ እና በኮሚሽን በጋራ ስብሰባ በ50% + 1 ድምጽ ለ6 ወራት ማራዘም ይቻላል። ስለጉባዔው መራዘም በወቅቱ ለአባላት እንዲያውቁ መደረግ |

| ተ.ቁ | አንቀጽ | መሻሻል ያስፈለገበት ምክንያት | የተሻሻሉ ድንጋጌዎች |
|---|---|---|---|
| | | | ይኖርበታል፣ ሆኖም ጉባዔውን ከ6 ወራት በላይ ማራዘም አይቻልም'' በሚል ተስተካክሏል፡፡ |
| 12. | " | አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ (3) ስለ ጉባዔው ፕሬዚዲየም አሰያየም በግልጽ አለቀመጡና ተግባርና ሃላፊነቱ በምርጫ ቦርድ እንዲቀመጥ አስተያየት በመቅረቡ፣ | ንኡስ አንቀጽ (4) – "ጉባዔው በፕሬዚዲየም ይመራል፣ የፕሬዚዲየሙ አባላት የፓርቲው ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንቶች ይሆናሉ'' በሚል ተስተካክሏል።<br>የፕሬዚዲየም አባላት ኃላፊነትና ተግባራት እንዲቀመጡ ተደርጓል። |
| 13. | **አንቀጽ 17 . . . የፓርቲው ጉባዔ ተግባርና ኃላፊነት** | 1. በንኡስ አንቀጽ (2) ስር.. "በሙሉ''…ውክልና ይሰጣል የሚለው መቀመጡ፣<br>2. በንዑስ አንቀጽ (1) (ሸ) ስር የሚመረጡ አባላት በልዩ ልዩ ምክንያት ቢጎድል የሚተካበት ስርዓት አለመኖር፣ | 1. ንኡስ አንቀጽ (2) – "በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጉባኤው ከተግባርና ኃላፊነቱ በከፊል ለብልጽግና ምክር ቤት ውክልና ሊሰጥ ይችላል'' በሚል ታርሟል፣<br>2. አዲስ ንዑስ አንቀጽ (3) - በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) (ቀ) ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንቶች በልዩ ልዩ ምክንያት ቢጎድል በብልፅግና ምክር ቤት ከሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይተካል'' በሚል ገብቷል። |
| 14. | **አንቀጽ 18 የፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ** | 1. ማዕከላዊ ኮሚቴ በፓርቲው ፕሬዚዳንትና በምክትል ፕሬዚዳንቶቹ በጋራ ይመራል ማለቱ ም/ፕሬዚዳንቶቹ አንዱ እንኳ ካልተገኘ መምራት አይችልም የሚል ትርጉም ያለው በመሆኑ ከአንቀጽ 21(1)(ሀ) ጋር የሚጋጭ መሆኑ፣<br>2. በንዑስ አንቀጽ (1) (ቀ) ስር የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት በልዩ ልዩ ምክንያት ቢጎድል የሚተካበት ስርዓት አለመኖር፣<br>3. የማ/ኮሚቴ አባል ስንብት ላይ ውሳኔ የሚሰጠው በጉባዔ ቢሆንም (17(1)(ረ) ማመልከቻ ስለመቀበል አለመቀመጥ፣ | 1. ንኡስ አንቀጽ (7) - የብልፅግና ምክር ቤት በፓርቲው ፕሬዝዳንት እና/ወይም በምክትል ፕሬዝዳንቶቹ በጋራ ይመራል'' በሚል ተስተካክሏል።<br>2. አዲስ ንዑስ አንቀጽ (ቀ) – "ከአባላቱ መካከል የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ይመርጣል፣ በልዩ ልዩ ምክንያት የተጓደሉትን ይተካል'' በሚል ታርሟል፣<br>3. አዲስ ንዑስ አንቀጽ (አ) – "በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 19(1)(ቀ) ከተመረጡ አካላት የሚቀርብ የመልቀቂያ ማመልከቻ ተቀብሎ ውሳኔ ይሰጣል'' በሚል ተቀምጧል፡፡ |

| ተ.ቁ | አንቀጽ | መሻሻል ያስፈለገበት ምክንያት | የተሻሻሉ ድንጋጌዎች |
|---|---|---|---|
| 15. | **አንቀጽ 19 የፓርቲ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ** | በንኡስ አንቀጽ (6)(ቀ) የፓርቲ ጉባዔ አዘጋጅ ኮሚቴ ውስጥ የኢንስፔክሽንና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን አለማካተቱ፣<br><br>የበዓል አዘጋጅ ኮሚቴ ተግባርና ሃላፊነት በምርጫ ቦርድ በግልጽ እንዲቀመጥ አስተያየት በመስጠቱ፣ | በንኡስ አንቀጽ (6) (ቀ) – "የፓርቲ ጉባዔ አዘጋጅ ኮሚቴ ከብልፅግና ምክር ቤት፣ ከኢንስፔክሽንና ከሥነ-ምግባር ኮሚሽን እና ሌሎች አግባቢነት ካላቸው አካላት በተውጣጣ አባላት ያዋቅራል" በሚል ተስተካክሏል፣<br>የጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴ ተግባራት እና ኃላፊነቶች እንዲቀመጥ ተደርጓል፤ |
| 16. | **አንቀጽ 21 የፓርቲው ፕሬዚዳንት ተጠሪነት** | በንኡስ አንቀጽ (1) ፕሬዚዳንቱ ተጠሪነቱ ለመረጠው አካልም ጭምር መሆን ሲገባ ለማዕከላዊ ኮሚቴ ብቻ አድረጎ ማስቀመጡ፣ | ንኡስ አንቀጽ (1) – "የፕሬዚዳንቱ ተጠሪነቱ ለጉባዔ እና ለብልፅግና ምክር ቤት ሆኖ… በሚል ታርሟል፡፡ |
| 17. | **አንቀጽ 23 በየደረጃው ኮሚሽን ስለማዋቀር** | 1. አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ (5)(ሀ) …*የኮሚሽን አባላት መጓደል ሲያጋጥም …ብቻ ተደርጎ መቀመጡ ክፍተት መሆኑ፣*<br>2. አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ (5)(ለ) እና በየደረጃው የሚገኘው የፓርቲ አካላት ምክረ ሃሳቡን ካልተቀመበ ምን ይሆናል የሚል አለመቀመጡ፣ | ንኡስ አንቀጽ (ሀ) – "… ወይም አዲስ ማቋቋም ሲያጋጥም ኮሚሽኑ ከየደረጃው ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ ጋር በመነጋገር ጊዜያዊ ምደባ ይሰጣል" ተብሎ ታርሟል፣<br>ንኡስ አንቀጽ (ረ) – "…እንዲሁም በኮሚሽኑ የሚቀርበውን የእርምት ሐሳብ አስተባባሪ ኮሚቴ ካልተቀበለው ኮሚሽኑ አንድ እርከን ከፍ ብሎ ላለው የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ ክስ ሊያቀርብ ይችላል" በሚል ታርሟል፡፡ |

| ተ.ቁ | አንቀጽ | መሻሻል ያስፈለገበት ምክንያት | የተሻሻሉ ድንጋጌዎች |
|---|---|---|---|
| 18. | 23 | በንኡስ አንቀጽ (6) (ሰ) የፓርቲውን ስነምግባር ያሻሽላል፣ ሙስናን መዋጋት ጥናቶችን ያደረጃል፣ ያስተባብራል የሚለው የግልጽነት መጓደል ችግር ያለበት መሆኑ፣ | 1. ንኡስ አንቀጽ (ሰ) - "የፓርቲው አባላትና አካላት የፓርቲውን ሥነ-ምግባር ማክበራቸውን ይከታተላል፣ የፓርቲ አባላትና አመራር ሊኖራቸው የሚገባ የፓርቲ ሥነ-ምግባር ከፓርቲ ጽ/ቤቶች ጋር ግንዛቤ ይሰጣል"፣<br>2. ንኡስ አንቀጽ (ሸ) – "ሙስና በፓርቲው ውስጥ ትግል ስለመደረጉ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣ የሙስና ጥፋቶች ሲፈጸሙ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከተው የፓርቲ አካላት ያቀርባል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል" እና<br>3. ንኡስ አንቀጽ (ቀ) – "የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ዙሪያ ጥናቶችን ያደርጋል" በሚል ተስረካክሏል። |
| 19. | 23 | በንኡስ አንቀጽ (6)(ሠ) (በ) እና (10) ምክረ/የውሳኔ ሀሳብ እንደሚያቀርብ የተቀመጠ ቢሆንም የአሰራር ስርዓት አለመዘርጋቱ፣ | • አዲስ ንኡስ አንቀጽ(10) – "በመ/ደንቡ በተሰጡት ተግባራትና ኃላፊነቶች አስመልክቶ የኮሚሽኑ በየደረጃው ከሚገኘው የፓርቲ ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ ጋር በየጊዜው በጋራ የሚወያዩበት መድረክ ይኖራል፣ የግንኙነት ጊዜውም የብልፅግና ምክር ቤት በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይሆናል" በሚል ተቀምጧል። |
| 20. | 23 | የኮሚሽን ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢና ጸሐፊ በፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ እንዲሳተፍ የአሰራር ስርዓት አለመካተቱ፣ | • አዲስ ንዑስ አንቀጽ (11) "የኮሚሽን ዋና ኮሚሽነርና ምክትል ዋና ኮሚሽነር በፓርቲው የብልፅግና ምክር ቤት ስብሰባ ያለ ድምጽ ይሳተፋል" በሚል ተቀምጧል፣ |
| 21. | 25 | አዲስ የተመሰረቱ ክልሎች በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ ማካተት አስፈላጊ በመሆኑ፣ | ንኡስ አንቀጽ (1)፡-<br>ቸ) በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት<br>ነ) በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት" ተጨምሯል። |
| 22. | **አንቀጽ 26 የፓርቲ** | 1. በንኡስ አንቀጽ (3) … የመሰረታዊ ድርጅት | • ንኡስ አንቀጽ (3) - "የብልፅግና ህብረት ኮንፈረንስ በየ3 ወር" ሆኖ |

| ተ.ቁ | አንቀጽ | መሻሻል ያስፈለገበት ምክንያት | የተሻሻሉ ድንጋጌዎች |
|---|---|---|---|
| | **ኮንፈረንስ የአሰራር ሥርዓቶች** | ኮንፈረንስ በየወሩ፣ በአደረጃጀት መመሪያ በየሶስት ወሩ የሚጋጩና ተግባራዊነቱ...<br>2. የአስተባባሪ ኮሚቴ እና የኢንስፔክሽንና የስነ ምግባር ኮሚሽን አባላት በኮንፈረንስ በቀጥታ የሚሳተፉ መሆኑ አለመቀመጡ፣<br>3. በየደረጃው የሚካሄዱ ኮንፈረንስ በማን እንደሚመራ አለመቀመጡ፣ | የብልጽግና ቤተሰብ ውይይት በአንድ ወር ይካሄዳል'' በሚል ተስተካክሏል፣<br>• አዲስ ንዑስ አንቀጽ (4) - ''የአስተባባሪ ኮሚቴ እና የኢንስፔክሽንና የስነ ምግባር ኮሚሽን አባላት'' በኮንፈረንስ በቀጥታ ይሳተፋሉ፣<br>• አዲስ ንዑስ አንቀጽ (5) - በየደረጃው የሚካሄዱ ኮንፈረንሶች በአስተባባሪ ኮሚቴ ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ይመራል'' በሚል ተቀምጧል:: |
| 23. | 26/27 | አንቀጽ 26(1) እና 27(6) እና 26(4) እና 27(5) ተመሳሳይ ድንጋጌ ሁለት ቦታ መቀመጡ፣ | አንድ ላይ በማጠቃለል እንዲቀመጡ ተደርጓል:: |
| 24. | **አንቀጽ 28 የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ** | ንዑስ አንቀጽ(5) በ **ለፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ** የፓርቲ መተዳደሪያ ደንብና መመሪያዎች በአግባቡ ስራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ አለመቀመጡ፣ | አዲስ ንዑስ አንቀጽ (5)(ሐ) – ''የፓርቲ መተዳደሪያ ደንብና መመሪያዎች በአግባቡ ስራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣሉ'' በሚል ተቀምጧል: |
| 25. | **አንቀጽ 29 በየደረጃዉ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች** | 1. በንዑስ አንቀጽ(4) ስር - የፓርቲ አባላት ኮንፈረንስ የማስተባበር ስራ በተግባር አለመቀመጡ፣<br>2. ቅ/ጽ/ቤቶች ፈሰስ የሚያደርጉት ገንዘብ (20%) አሰራር ግልጽነት አለመኖር፣<br>3. በንዑስ አንቀጽ (4)(ለ) ላይ - የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱን ሂሳብ በየዓመቱ በውጭ የሂሳብ ኦዲተር እንዲመረመር ያደርጋሉ ተብሎ አለመቀመጡ፣<br>4. የፓርቲ መተዳደሪያ ደንብና መመሪያዎች በስራ ላይ የማዋል እና ሪፖርት ለአስተባባሪ ኮሚቴ እንደሚያቀርቡ አለመቀመጡ፣ | አዲስ ንኡስ አንቀጽ(ለ) ''ለ) የፓርቲ አባላት ኮንፈረንስ ያስተባብራሉ''<br>አዲስ ንዑስ አንቀጽ (መ) – ''የፓርቲው ብልፅግና ምክር ቤት በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰነው ድርሻ መሰረት ከገቢያቸው ፈሰስ ያደርጋሉ፣<br><br>አዲስ ንዑስ አንቀጽ (ሠ) – ''የቅ/ጽ/ቤቱን የሂሳብ መዛግብት እና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየወቅቱ በውስጥ ኦዲት እና የዓመቱ በውጭ ኦዲተር የበጀት ዓመቱ አልቆ በ3 ወር ውስጥ እንዲመረመር ያደርጋሉ'' በሚል ተቀምጧል፣<br><br>አዲስ ንዑስ አንቀጽ (በ) – ''የፓርቲ መተዳደሪያ ደንብና መመሪያዎች በስራ ላይ ያውላሉ፣ ለአባላትና ለአመራር ግንዛቤ ይፈጥራሉ'' በሚል ተቀምጧል፣<br>በንኡስ አንቀጽ (ነ) ''...አስተባባሪ ኮሚቴ... ያቀርባሉ'' በሚል ተቀምጧል:: |

| ተ.ቁ | አንቀጽ | መሻሻል ያስፈለገበት ምክንያት | የተሻሻሉ ድንጋጌዎች |
|---|---|---|---|
| 26. | **አንቀጽ 30-31 ሊጎች** | 1. ሊጎች የሚመለከት የፓርቲ ፕሮግራም እንደሚያስፈጽሙ በግልጽ ባለመቀመጡ የራሳቸውን ፕሮግራም እስከ ማውጣትና ማጽደቅ የደረሱ መሆኑ፣ | 1. በአንቀጽ 32 እና 33 ንዑስ አንቀጽ (3) በተመሳሳይ … "የፓርቲ አሳቤዎች፣ ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብና መመሪያዎች ተገዥ እና የማክበር ግዴታ አለባቸው፣ ክንፎቹ ፕሮግራም አይኖራቸውም፣ በሚል ተቀምጧል፣ |
| 27. | **አንቀጽ 34 የፓርቲ ሀብት የአሰራር ሥርዓት** | በንዑስ አንቀጽ(1) ስር - የበጀት አስተዳደር፣ የኦዲት፣ የግዥ፣ ሰነዶች… አለመካከተቱ፣<br>የፓርቲ ሰነዶች አጠባበቅና አጠቃቀም ሥርዓት አለመኖር፣<br>የሊጎች ፋይናንስ አጠቃቀም ግልጽ አለመሆን፣ | • ንኡስ አንቀጽ (1) – "በበጀት አስተዳደር፣ ሰነዶች እና የግዥ" እንዲካተቱ ተደርጓል፣<br>• አዲስ ንዑስ አንቀጽ (2) - የፓርቲ ሰነዶች በፓርቲው ምክር ቤት በሚወጣ መመሪያ በአግባቡ መጠበቅ አለባቸው፣<br>• አዲስ ንዑስ አንቀጽ (6) - "*የክንፎቹ ፋይናንስ በፓርቲ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት ይመራሉ" በግልጽ መቀመጥ አለበት"* በሚል ተቀምጧል:: |
| 28. | **አንቀጽ 38** የፓርቲው አማካሪ የመማክርት ጉባዔ | ስያሜው አወዛጋቢ በመሆኑ እና ከፓርቲ የሚሰናበቱ አመራሮችና አባላት የሚካተቱበት ስርዓት አለመኖሩ፣ | 1. አንቀጹ - የፓርቲው አሰላሳይ ቡድን (Think Tank) በሚል ተተክቷል፣<br>2. አዲስ ንኡስ አንቀጽ (2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ከፓርቲ በክብር እና በፍቃደኝነት የተሰናበቱ አሰላሳይ ቡድን አባል ሊሆኑ ይችላሉ::<br>3. አዲስ ንኡስ አንቀጽ (4) የፓርቲው አሰላሳይ ቡድን የአሰራር ስርዓት በፓርቲው ዋና ጽ/ቤት ሊዘረጋ ይችላል:: |
| 29. | **አንቀጽ 39 የመተዳደሪያ ደንብ የበላይነት** | በፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ እና መመሪያዎች ትርጉም መካከል ግጭት ቢፈጠር የትኛው ተቀባይነት ያለው ቅጅ መሆኑ አለመገለጹ፣ | አዲስ ንዑስ አንቀጽ (3) – "በጉባዔው በጸደቀው መተዳደሪያ ደንብ ቅጅ ወይም በማዕከላዊ ኮሚቴ በጸደቁት መመሪያዎች እና በተለያዩ የፓርቲ ቋንቋዎች በተተረጎሙ ሰነዶች መካከል ግጭት ሲፈጠር ለጉባዔው ወይም ለብልፅግና ምክር ቤት ቀርቦ የጸደቀው የሰነድ ቅጅ የበላይነት ይኖረዋል" በሚል ተቀምጧል:: |

| ተ.ቁ | አንቀጽ | መሻሻል ያስፈለገበት ምክንያት | የተሻሻሉ ድንጋጌዎች |
|---|---|---|---|
| 30. | **አንቀጽ 41 መተዳደሪያ ደንቡን ስለማሻሻል፣ መቀየርና ስለመሻር** | በፓርቲው 1ኛ ጉባዔ የጸደቀው መተዳደሪያ ደንብ በግልጽ የተሻረ እና የተተካ መሆኑ መግለጽ በማስፈለጉ፣ | አዲስ ንዑስ አንቀጽ (5) – ‘‘በብልፅግና ፓርቲ አንደኛ መደበኛ ጉባዔ ጸድቆ የነበረው የመተዳደሪያ ደንብ ተሽሮ በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ተተክቷል’’ በሚል ተቀምጧል፡፡ |